# መንፈስ ቅዱስ ከማን ሠረጸ ?

(ከሲራክ ገ/ክርስቶስ)

በዚህ በያዝነው ርእስ ባለፈው ዕትማችን እንደተገለጸው በዓለም አቀፋዊው የሲኖዶስ ውሳኔ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረጹን ተመልክተናል። ተከታዩን ክፍል ይዘን እንደምን ቀርብ ቃል መግባታችንን እናስታው ሳለን። የአበው ሊቃውንት አምላክ ምሥጢሩን ይገልጽልንና ከዚህ እንደሚ ቀጥለው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርጸት የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ታሪካዊ አመጣጥ እናያለን።

እግረ መንዳችንን ከሕትመት ግድፈት የተነሣ በስሕተት ባለፈው ዕትም በገጽ ፲፮ በመጀመሪያው ዓምድ ከመስመር ፳፭–፳፱ "እግዚአብሔር ወልድም ለዘላለም በሠራጺነት ግብሩ ይኖራል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ለዘላለም በተወላዲነት ግብሩ አለ ይኖራል።" ተብሎ ተጽፏል። ትክክለኛው መኾን የነበረበት "እግዚአብሔር ወልድም ለዘላለም በተወላዲነት ግብሩ አለ ይኖራል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ለዘላለም በሠራጺነት ግብሩ አለ ይኖራል።" ነው።

በተጨማሪም በገጽ ፲፮ በመሥመር ፴፫ ሥርጸት /procesoion/ በማለት በስሕተት የተጻፈው ሥርጸት /procession/ ተብሎ ታርሟል።" መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረጹን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሌሎች እህት የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ጋር በኅብረት በመኾን ትቀበላለች። ኦሪየንታል /የምሥራት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ/ አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉት የእስክንድርያ፣ የኢትዮጵያ፣ የሶርያ፣ የአርመንያና የሕንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። የኦርየንታል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዓለም አቀፋዊ የቤተክርስቲያን ሲኖዶሳዊ ውሳኔ መሠረት ይኸውም በኒቅያ ጉባኤና በቁስጥንጥንያ ጉባኤ የተወሰነውን የሃይማኖት ቀኖና በመቀበላቸው ስለ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረጽ ያላቸው እምነት እስከ ዛሬ ጸንቶ አለ ይኖራል።

ኬልቄዶናውያን የምዕራብ የሮማ ካቶሊክና የምሥራቅ የግሪክ ኦርቶዶክስ ወገኖችም የኒቅያውንና የቁስጥንጥንያውን የጸሎተ ሃይማኖት ውሳኔ በመጀመሪያ ተቀብለው ይኖሩ ነበር። በኋላ ግን የሮማ ካቶሊካዊት ጉባኤ ቀኖናውን ሽራ በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተክርስቲያን የሌለውን ቀኖና ጨምራ ዘሠረፀ እምወልድ "ከወልድ የሠረፀ" በማለቷ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ከግሪክ ኦርቶዶክስም ለይቷት ይኖራል።

በጸሎተ ሃይማኖትም ኾነ በመጽሐፍ ቅዱስ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ከአብ ብቻ መኾኑ እየታወቀ የሮም ካቶሊክ ማኅበር እንደ እ·ዘ·አ· በ፭፻ ፮ ዓ·ም እንደ እ·ዘ·አ· በ፩፻፲፬ ዓ·ም "ከወልድም ሠረፀ" በማለቷ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ተለየች። ይህ በታሪክ ኬልቄዶናውያን በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ ተወጋግዘው የተለያዩበት ወቅት ነው። በዚህ ክርክር ውስጥ ኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተሳታፊዎች አል ነበሩም ምክንያቱም ከመጀመሪያውኑ ኬልቄዶናውያን ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ባሕርይ ባዮች ስለ ኾኑ ተለያይተዋልና ነው። ኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት በምሥጢረ ሥጋዌ ያላቸው እምነት ክርስቶስ መለኮቱ ከትስብእቱ በባሕርያዊ ተዋሕዶ አንድ ስለኾነ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ብለው የምንታዌን ትምህርት ያወግዛሉ። ከላይ እንደተገለጸው በምሥጢረ ሥላሴም ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት ያላቸው እምነት በጸሎተ ሃይማኖትና በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተደነገገው "ዘሠረጸ እምአብ ከአብ የሠረጸ" በማለት ነው። ይኸውም በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ።

<u>ከአብ የሠረጸ</u> ከአብና ከወልድ ጋራ በአንድነት እንሰግድለታለን። "ጸሎተ ሃይማኖት ዘኒቅያ" ወሰበ መጽአ ጰራቀሊጦስ ዘአነ እፌኑ ለክሙ ዘይወጽእ እምአብ ውእቱ ሰማዕትየ" ከአብ የሚወጣ እኔ የምልክላችሁ ጰራቀሊጦስ በመጣ ጊዜ ምስክሬ ነው። /ዮሐ ፲፭፥፳፮/ ተብሎ እንደተጻፈው ነው።

በቁስጥንጥንያዊት የግሪክ ኦርቶዶክስና በምዕራብ የሮማ ካቶሊካዊት ጉባኤ መካከል የመንፈስ ቅዱስን ሠራጺነት በተመለከተ ተነሥቶ የነበረው ውዝግብ በውጭ ቋንቋ ፊሊዩክ ኮንትሮቨርሲ /FILOQUE CONTROVERSY/ ተብሎ ይታወቃል። ፊሊዩክ /FILOQUE/ ላቲናዊ ቃል ነው። ትርጉሙም and from the Son "ከወልድም ሠረጸ እንደማለት ነው። ይህ የዶግማ ፎርሙላ /የሃይማኖት ውሳኔ/ መንፈስ ቅዱስ ሁለት ጊዜ እንደ ሠረጸ ይገልጻል። በኒቅያና በቁስጥንጥንያ የሃይማኖት መግለጫ ላይ በጸሎት ሃይማኖት ማለት ነው። ምንም እንኳን በምዕራብ የካቶሊካዊት ማኅበር "ከአብ የሠረጸ" በሚለው ሐረግ ላይ የጨመረችው ቃል ነው። ምንም እንኳን



www.ethiopisnorthodox.org

በምዕራብ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት በይፋ "ከወልድም ሠረጸ" የሚለው ቃል በዐሥራ አንደኛው ምዕተ ዓመት የተጨመረ መኾኑ ቢታወቅም የታሪኩ መንሥኤ ወደ ኋላ ሄዶ በስድስተኛው ምዕተ ዓመት ላይ ያርፋል። ሐሳቡ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈለቀው በስፓኝ ግዛት ነው። የስፓኝ ቤተክርስቲያን በአርዮሳውያን ላይ ያላትን ተቃውሞ ለማጠናከር ስትል የወሰደችው አቋም ነው። ይኸውም ወልድ ከአብ ጋር እኩል ነው ምክንያቱም ለመንፈስ ቅዱስም መገኛ ነውና ስለዚህ ከአብ የሚያንስበት አንዳች ሰበብ የለም በማለት ወልድ ከአብ ጋር ትክክል መኾኑን ያመለክታል ስትል ተጠቅማበታለች።

እንደ ኤውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር በ፭፻፹፱ ዓ.ም የእስፓኝ የቶሌዶ ሪካርድ ጉባኤ የውግዘት ረቂቅ" በመንፈስ ቅዱስ የማያምን ወይም ከአብና ከወልድ መሥረጹን የማያምንና ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት ለዘለዓለማዊና እኩል መኾኑን የሚክድ ቢኖር የተወገዘ /የተለየ/ ይሁን" በማለት ፊልዮክን ያጸድቃል፤ ዘሠረጸ እምወልድ" ሲል ይገልጸል ይህ በኒቅያና ቁስጥንጥያ የሃይማኖት ቀኖና የሌለ ጭማሪ ፊልዮክ የተባለው ቃል ከእስፓኝ ወደ ፈረንሳይ ተዛመተ ከዚያም ወደ ጀርመን አምርቶ ከ፯፻፺፬-፰፻፲፬ /በቻርልማኝ ተቀባይነት አገኘ በተጨማሪም በ፯፻፺፬ ዓ.ም በፍራንክፈርት በተደረገው በሴሚ አይኮኖክላስት ጉባኤ /Semi-Iconoclast Council/ተቀባይነት ማግኘቱ ተረጋገጠ በቻርለማኝ ችሎት የነበሩት ጸሐፊዎች «ፊልዮክን» ለመጀመሪያ ጊዜ የክርክር አጀንዳ አደረጉት። ግሪኮች ይህ መናፍቅነት ነው ብለው ቢከሷቸው በአጸፋው የችሎቱ ጸሐፍትም ግሪኮችን አዲሱን ውሳኔ ሳይቀበሉ በጥንቱ የሃይማኖት ቀኖና ሥርዓት አምልኮአቸውን በመፈጸማቸው በተመሳሳይ ከሰሷቸው። የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ፎቲየስ በ፱ኛው ምዕተ ዓመት እንደገለጸው የፊልዮክ ስርጭት ቡልጋሪያ፤ በፈረንሳይ ሚሲናውያን አማካይነት ሊገባና ሊተዋወቅ እንደቻለ ገልጸዋል። ይኸውም ሊሆን የቻለው ቡልጋሪያውያን በቅርብ ጊዜ በግሪኮች አማካይነት ተሰብከው የግሪክ ኦርቶዶክስ ክርስትናን በመቀበላቸውና በቢዛንታይን ፓትርያርክ ሥር መዋላቸው ስለታወቀ ይኽንን ለማክሸፍ በሚሲዮናውያን አማካይነት የተወሰደ ፀረ-ቢዛንታይን ቅስቀሳ ነበር። ክርክሩ በጀርመንና በቢዛንታይን መካከል ስለቀጠለ ሮማ ሽምግልና ያዘች በ፰፻፰ ዓ.ም ፓፓ ልዮን ሣልሳዊ /፯፻፺፭-፰፻፲፮ ዓ.ም/ ለቻርልማኝ ደብዳቤ እንዲህ ሲል ጻፈለት "ምንም እንኳን ራሴም ብሆን የትምህርትነቱን ጤናማነት ብቀበልም ፊልዮክ ከጥንቱ የቤተክርስቲያን ቀኖና ጋር ስለሚቃረን ስሕተት እንደኾነ እገነዘባለሁ" አለ ፓፓ ቤኔዲክት ሳምናዊ /፲፻፲፪-፲፻፳፬ ዓ.ም/ በመጨረሻ ፊልዮክን ስላጸደቀ በሥልጣኑ ተቀባይነት እንዲኖረው ስለወሰነ በምዕራብና በቢዛንታይን አብያተ ክርስቲያናት ታላቅ መከፋፈልን ፈጠረ ሁለቱም ክፍሎች ተወጋግዘው ተለያዩ። እንግዲህ ከኒቅያናቁስጥንጥንያ የሌለ በጸሎተ ሃይማኖት ላይ የሮማ ካቶሊክ የጨመረችው ከዓለም አቀፋዊውም የቤተክርስቲያን ቀኖና ውጭ ስለሆነ "መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ሠረፀ" የሚለውን የፊልዮክ አስተሳሰብ መቀበል መናፍቅነት መሆኑን ያመለክተናል። ቤተክርስቲያናችን የፊልዮክን መጨመር አትደግፍም፤ በኒቅያ-ቁስጥንጥንያ ውሳኔ ጸንታ"ዘሠረፀ እምአብ" ብላ ስትመሰክር ትኖራለች።

የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የፊልዮክን ሐሳብ ተቀብላ በጸሎተ ሃይማኖት ላይ የደረበችው ዘግይታ ከመኾኑም በላይ ቀደም ሲል የነበሩት ፓፓዎቿ ግን ይኽን ሐሳብ ሲቃወሙት እንደነበር የታሪክ ምስክርነት አለ። ስምንተኛው መቶ ዘመን ማብቂያ ላይ ሉክዮስ የተባለ መናፍቅ ተነሳ በቁስጥንጥንያ ፻፶ ሊቃውንት በወሰኑት ዘሠረፀ እምአብ ሚለው የሃይማኖት ውሳኔ ላይ "ዘሠረጸ እምወልድ" ሲል ፊልዮክን ጨመረ በሰይጣን ምክር ተነሣሥቶ ኑፋቄውን ለማሰራጨት በኢየሩሳሌም አውራጃ እየተመላለሰ ማስተማር ጀመረ ቅዱስ ጐርጐርዮስ ኢየሩሳሌም ለመሳለም ሄዶ ነበርና የከሐዲውን ቃል ሰምቶ በአባታዊ ምክር ገሰጸው ያም ከሃዲ ሰው እምቢ አልሰማም ብሎ በግትንነት ወደ ሮም ሄዶ ትምህርቱን ሲነግራቸው የሮሚ ሰዎች አክብረው ተቀበሉ። ከዚህ በኋላ ወደ ፈረንሣይ ሄዶ ለንጉሡ ለታላቁ ካርሎስ ክህደቱን ሰበከለት ሰይጣናዊ ስብከቱን ንጉሡ እንደተቀበለው አይቶ ጉባኤ ይደረግልኝ ሲል ለመነው። ንጉሡም እንደሰማ ጉባኤ አላደርግም ብሎ ወደ ሮሚ ጳጳስ ወደ ፫ኛ ልዮን ከሚባል ላከ ልዮንም ይህ ክሕደት አዲስ ኑፋቄ ነውና አልቀበልም ብሎ ወደ ንጉሥ ምላሽ ሰደደ ወዲያውም እንዲህ አደረገ በ፫ቱ ዓበይት ጉባኤ አበው ቅዱሳን ሊቃውንት የወሰኑትን የኒቂያ፤ የቁስጥንጥንያና፤ የኤፌሶንን ውሳኔ

## ማረሚያ

በ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ዕትማችን በውኑ ታቦት ጣዖት ነውን? በሚለው ርዕሳችን ሥር ቀርቦ በነበረው ጽሑፍ ገጽ ፬ ላይ በቁጥር ፲፩ መግለጫ ላይ "በታቦትና በጣዖት መካከል ያለው ብሎ ሃሳቡን ሳይጨርስ ወደ ቁጥር ፲፪ ጽሑፍ ይገባና" በዘመነ ሐዲስ ታቦት ..... ብሎ የጀመረው ጽሑፍ .... ምክንያቱም ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሚፈተትበት መንበሩ ነውና። ብሎ ያጠቃላል። በቀጣዩ መስመር "ልዩነት በብርሃንና በጨለማ መካከል .... በማለት የሚጀምረው ጽሑፍ የቁጥር ፲፩ ተከታይ መሆኑን እየገለፅን ጹሑፍ "ዳጎንን የገለበጠ አምላክ ዛሬም አስተሳሰባቸውን እንደሚገለብጠው እናምናለን።" በማለት የሚጨርስ መሆኑን በትህትና እናሳስባለን።



www.ethiopisnorthodox.org

በላቲንና በዮናኒ ቋንቋ በሁለት ሰሌዳ ላይ አስቀርጾ በቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል ደጅ ሰቀላቸው የሚገባወም የሚወጣውም ሁሉ ተመልክቶ ከአዲሱ ኑፋቄ እንዲጠበቅ ነግዝት በርግማን ወስኖ አኖራቸው።

ሁለተኛም በ፰፻፶፮ ዓ·ም የተሾመው ፓፓ በናድክቱስ ሣልሳዊ ወደ ምሥራቅ ሊቃነ ጳጳሳት /ወደ ቢዛንታይን/ እንዲህ ሲል ላከ "መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ይሠርፃል እንጂ ከወልድ አይሠርፅም። ይህን በተቀደሱት ጉባኤዎች የተወሰነውን ሃይማኖት ከሚጠብቅ በቀር የሮሜ ካህናትና አለቆች ከማንም ጋር አይሳተፉም የጥፋት ልጆች መንፈስ ቅዱስ ከወልድም ሠረፀ ያሉትን የሚቀበል እንደ እነርሱ ርጉም ይሁን" የሚል ነበር።

ሦስተኛም በሮሜ በ፰፻፸፱ ዓ·ም የተሾመው ስምንተኛ ዮሐንስ የሚባለው ፫፻፹፫ ኤጲ.ሲ ቆጳሳትን ሰብስቦ እንዲህ አለ። "አስቀድሞ በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ከወሰኑት ሌላ አሁንም እፊታችን ከተነበበው በቀር ደፍሮ አዲስ ሃይማኖት ቢያወጣ እምነት ነው ብሎ ቢይዘው መንፈሳውያን አበው ከደነገጉት ላይ የሚጨመር የሚያጐድል ቢገኝ ካህን እንደሆነ ክህናቱን እንሽረዋለን ምዕመንም ቢሆን ገዝተን እንረግመዋለን ከእኛ በፊት የነበሩት ጉባኤዎች ያደርጉት እንደነበረ" ብሎ የግዝት ውሳኔ በማስተላለፍ "ከወልድ ሠረፀ" የሚል ውጉዝ መኾኑን ገልጠዋል።

ከዚህ በላይ ታሪካዊ መረጃዎችን በማቅረብ እንደተነተነው የፊሊዩክ በጸሎተ ሃይማኖት ላይ መጨመር ትክክለኛ አለመሆኑን ያሳውቀናል ስለኾነም መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ እንደሠረፀ እናምናለን እንጂ ጭማሪውን ከወልድም ሠረፀ የሚለውን ሐረግ መቀበል አንችልም ግዝት ነው አይገባም።

የፊልዩክን መጨመር በተመለከተ ጭማሪውን በመቃወም ረገድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለምን እንደማይቀበሉ የሚያቀርቡት መረጃ ምን እንደሆነ እንደሚከተለው እንገልጸለን።

(የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን ስንል የኦሪንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስን ያጠቃልላል። ኬልቄዶንያውያን ያልሆኑትንና የሆኑትን ያቅፋል።)

፩/ ጌታ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረፁን /መውጣቱን/ አረጋግጦልናል /ዮሐ ፲፭ቁ ፳፮/ ስለኾነም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረፁን ያምናሉ። መንፈስ ቅዱስ ከወልድ እንደሠረፀ ክርስቶስ ያልገለጸው አንዳንዶች እንደሚያስቡት ለትሕትና ብሎ አይደለም። ለትሕትና ቢሆንማ ኑሮ ጰራቅሊጦስን /አጽናኙን/ እልክላችኋለሁ ባላለም ነበር። ባለማለቱ ለትሕትና ሳይኾን መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ሠረፀ ያላለው መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረፁን ለማስረዳት በመፈለጉ ነው። መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ ካለ ዘንድ እውነት ቢሆን ኑሮ ከእኔ የሠረፀውን ይል ነበር እንጂ ከአብ የወጣውን /የሠረፀውን/ ብሎ ብቻ ባልተናገረም ነበር።

፪/ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የፊልዩክ መጨመር አግባብ አለመሆኑን አበክራ የምትቃወምበት ምክንያት በሃይማኖታዊ ቀኖናዎቿ ከጥንት ጀምሮ በትምህርቷም ሆነ በታሪካዊ ጉዞዋ የሌለ በመኾኑ ነው። በጥንት ሃይማኖታዊ ቀኖናዎቿም ሆነ በሥርዓተ አምልኮዋ የፊልዩክ ምልክት ተጨምሮ በአንድም መግለጫ ታቅፎና ታክሎ አይገኝም።

፫/ የሥላሴን አካላት መኖር በሚመለከት ጥንታውያን የቤተክርስቲያን አባቶች ሲገልጹ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረፁን አረጋግጠዋል። ጥቂቶቹን የአበው መግለጫ እንመልከት


* «ቅዱስ መንፈስ አውነተኛ መንፈስ» ነው ከአብ በእርግጥ ይወጣል መገኘቱም እንደወልድ ተወልዶ አይደለም በመሠረፅ ነው እንጂ
(ቅዱስ ጐርጐርዮስ ዘእንዚነዙ)

* «የአብ አካላዊ ግብር የወልድን የመንፈስ ቅዱስን ግብር ለመኾን አይለወጥም አስገኝ ምክንያት ሳይኖረው በአስገኝነት /በመሠረትነት/ መኖር የአብ የብቻው ጠባይ ነው። ይህ የአስገኝነት ጠባይ ለወልድ ወይም ለመንፈስ ቅዱስ አይሆንም። ምክንያቱም ወልድ ከአብ ይወጣልና /ይወለዳልና/ መንፈስ ቅዱስም ከእግዚአብሔር አብ ይወጣል /ይሠርፃል/ እንዲህ እንደኾነ ቅዱሳን መጻሕፍት ይመሰክራሉ።» /ዮሐ ፲፮፥፳፰ ዮሐ ፲፭፥፳፮/ (ቅዱስ ጐርጐርዮስ ዘኑሲስ)

*

የእስክንድርያው ቅዱስ አትናቴዎስና ቅዱስ ባስልዮስ በግልጽ «መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሠርጻል» ሲሉ ወልድን ሳይጠቅሱ ጽፈዋል።

ምንም እንኳን የፊልዩክ በሃይማኖት ቀኖና ላይ መታከል ትክክለኛ አለመኾኑ በትምህርተ መለኮት በቀኖና ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት የለሽ እንደኾነ የታወቀ ቢኾንም የፊልዩክ ደጋፊዎች ፍንከች አንልም በማለት ይሟገታሉ። ለምሳሌ ያህል





www.ethiopisnorthodox.org

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዶችን ጥቅሶች እየለቀሙ በሚሰጡት የተሳሳተ አመለካከት ላይ ጥቂት ማብራርያ መስጠት ይገባልና እንመልከት።

ሀ/ "ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና" /ዮሐ ፲፮ቁ፲፬/ ይኸን ይዘው ጥቅሱ መንፈስ ቅዱስ ከወልድም የሠረፀ መኾኑን የሚያመለክት ነው ይላሉ። ቃሉ ግን እንዲህ አይልም ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል ማለቱ እኔ የነገርኳችሁንና የረሳችሁትን ያስታውሳችኋል። ሳልነግራችሁ የቀረሁትንም በመለኮታዊ አንድነታችን እኔ የማውቀውን ኹሉ እርሱም የሚያውቅ እንደመኾኑ እኔ የምነግራችሁን ያኽል እርሱም ይነግራችኋል ማለቱ ነው። በተጨማሪም መውሰድ ማለት መሥረጽ (መውጣት) ተብሎ ሊተረጉም አይችልም። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ቃልነትን ገንዘብ አድርጎ በወልድ ቃልነት ያስተምራል በጌትን በመምህርነት ከወልድ ጋር አንድ ስለኾነ የወልድ ገንዘብ ሁሉ ለመንፈስ ቅዱስም ገንዘቡ መኾኑን ያመለክታል። ተብሎ ይተረጐማል እንጂ ከወልድ ሠረጸ አያሰኝም።

ለ/ ስለ መንፈስ ቅዱስ "የልጁ መንፈስ" "የክርስቶስ መንፈስ"፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ" ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ ፬ ቁጥር ፮፣ሮሜ ፰–፱፣ ፊሊጵ ፩፥፲፱ የተናገረውን ቃል ይዘው መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ሠረጸ ይላሉ። እነርሱ አሉ እንጂ ጥቅሱ አያስረዳቸውም። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ አነጋገሩ ወልድ ለመንፈስ ቅዱስ መገኘት ምክንያት ነው ለማለት አልጠቀሰውም። እርሱ ለማለት የፈለገው መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ጋር በሕልውና የተገናዘበ በባሕርይ አንድ የኾነ ከወልድ ጋር አንድነት ያለው ነው ብሎ ለመግለጽ ነው።

"የልጁ መንፈስ" የሚለው ሐረግ የሚያስረዳን መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ጋር አንድ ዓይነት ባሕርይ ያለው በባሕርይ ክብሩ ምስጋናው ጌትነቱ አገዛዙ ሁሉ ከወልድ ጋር እንደወልድ ትክክል ክብር ያለው መኾኑን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ጋር በክብር አንድ ዓይነት ባሕርይ እንዳለው ለመግለጽ ተናገረ እንጂ የሥርጸቱን መንሥኤ ምክንያት ለማመልከት አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ የጥበብ መንፈስ፣ የማስተዋል መንፈስ፣ የእውቀት መንፈስ፣ የፍቅር መንፈስ ራስን የመግዛት መንፈስ፣ የልጅነት መንፈስ" ተብሎ ይጠራል። /ኢሳ ፲፩ቁ፪፣፪ኛ ጢሞ ፩ቁ፯ ሮሜ ፰ቁ፲፭/ ወዘተ እንዲህ ስለተባለ ግን መንፈስ ቅዱስ ከጥበብ ከማስተዋል ከእውቀት ከፍቅር ራስን ከመግዛትና ከልጅነት ሠረጸ ማለት አይደለም። ከላይ የልጁ መንፈስ" የተባለውም ጥቅስ በዚሁ መልክ መታየትና መተርጐም ይኖርበታል።

ሐ/ በዮሐንስ ወንጌል ስለመንፈስ ቅዱስ መላክ መሰጠት ተነግሮዋል

፩/"ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" /ዮሐ ፲፬ቁ፲፮/

፪/ "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ" /ዮሐ፲፭ቁ፳፮/

፫/ "እኔ ብሄድ ግን እርሱን /ጰ ራቅሊጦስን/ እልክላችኋላሁ" /ዮሐ ፲፮ቁ፯/

በመንፈስ ቅዱስ መላክ /ተፈናዊነትና/ በሠራጺነቱ መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ መታወቅ አለበት። መንፈስ ቅዱስ ከአብ የመሥረጹ ሥራ ዘላለማዊነት ያለው የአካሉ ግብር ሲኾን የተፈናዊነቱ/ የመላኩና የመሰጠቱ/ ነገር ማለትም በበዓለ ሃምሳ በሐዋርያት ላይ የማደሩ ሥራ በውሱን ጊዜ ውስጥ የተከናወነ የመለኮታዊ ቃል ኪዳን ፍጻሜ ማግኘት ስለኾነ ሠራጺነቱንና መላኩን አንድ አድርጎ ማየት ስሕተት መኾኑ መታወቅ አለበት። በማጠቃለያው መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ መሥረጹን ዐውቀን በኋላ የመጣውን ኑፋቄ ከመቀበል ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ያድነን ይጠብቀን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ከረሀብ ነፍስ ድነን ሌሎችን ለማዳን እንነሳ

ሰው ከፀሐይ በታች ካሉት ፍጥረታት ተለይቶ እንደ ሰማያውያን መላእክት ፈጣሪውን ዐውቆ እንዲያመልከው፣ እንዲገዛለት ተፈጥሮአል። እንደ እንስሳት ሥጋዊ ፈቃድ ቢኖረውም እንደመላእክት ደግሞ መንፈሳዊ ፍላጐት አለው። የደቂቀ አዳምን ታሪካዊ ሂደት ስንመረምር ከእንስሳት ልዩ የሆኑበትን ምክንያት ተረድተናል። እንስሳት በደመ ነፍስ ሕያዋን ሁነው እንደዐቅማቸው ደማዊት ዕውቀት ቢኖራቸውም እንደሰው የአምልኮት ሥርዓት እንደሌላቸው ማንም ይረዳዋል። ሰው ብቻ ከእነርሱ ተለይቶ በማንኛውም የታሪክ ዘመኑ ያለ አምልኮት ኖሮ አያውቅም።

እንስሳት የሚነጩት ሣር፣ የሚቀነጥቡት ቅጠል፣ የሚልሱት ደም፣ የሚግጡት አጥንት፣ የሚጐነጩት ውሀ ካገኙ ስለሌላው ነገር እንደ ሰው ሲጨነቁ አይገኙም። ምክንያቱም ተፈጥሮአቸው ከሥጋ ብቻ በመሆኑ ነው። ሰው ግን በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረች ለባዊት ነባቢት ሕያዊት ነፍስ ስላለችው ምንጊዜም ቢሆን በሥጋዊ ነገር ብቻ አይረካም። ምክንያቱም ተፈጥሮው ከሥጋ ብቻ ሳይሆን ከረቂቅ ነፍስም የተሠራ በመሆኑ ነው።

በቅዱስ ወንጌል እንደተፃፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት ስለ እኛ ጾሞ፣ በተራበ፣ ጊዜ በስስት የመጣውን ፈታኝ በትዕግስት ድል ነስቶ ካባረረው፣ በኋላ በጾም ኃይል መኖር እንደሚቻል ለክርስቲያኖች ትምህርት



www.ethiopisnorthodox.org

ሰጥቷል። "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" ብሏል ማቴ ምዕ ፬ ቁ ፬ ከዚህ ኃይለ ቃል ለመረዳት የምንችለው የሰው ሕይወቱ በምግበ ሥጋ ብቻ ሊሟላ እንደማይችልና ኑሮው ጐዶሎ እንደሆነ ነው። የሰው ኑሮው ሙሉ የሚሆነው ምግበ ነፍስ ቃለ እግዚአብሔርን በመመገብ ስለሆነ፣ ነፍሱ እንድትረካለት በሕገ እግዚአብሔር በትእዛዘ እግዚአብሔር መመራት ይኖርበታል። ከመንፈሳዊ ትምህርት በራቀ ቁጥር በነፍሱ በኩል ከባድ አደጋ ይደርስበታል፣ ይህም አደጋ ለሥጋውም ተርፎ ሲያስጨንቀው ይኖራል። የመንፈስ ረሀብና ጥማት በዓለም ላይ እንደሚመጣ ነቢዩ አሞጽ ትንቢት ተናግሯል በዚህም ጠንቅ ወጣቶችና ደናግል ሞተ ነፍስ ይደርስባቸዋል። "እነሆ በምድር ላይ ራሀብን የምሰድብት ዘመን ይመጣል ይላል ጌታ እግዚአብሔር እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም። ከባሕርም እስከ ባሕር ድረስ ከሰሜንም እስከ ምሥራቅ ድረስ ይቅበዘበዛሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለመሻት ይሯሯጣሉ አያገኙትም በዚያ ቀን መልካሞች ደናግል ጐበዛዝትም በጥም ይዝላሉ" አሞጽ ምዕ ፰ቁ፲፩–፲፫

ይኽን ትንቢት በአትኩሮተ ኀሊና ስንመረምረው ከምንጊዜውም ይልቅ በያዝነው ምዕተ ዓመት በሥራ ተተርጉሞ ወይም ተፈጽሞ እናገኘዋለን። ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ከተመሠረተች ዘመናት አልፈዋል። ጥንታውያን የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በየመቃብር ቤቱ በየገዳማቱ ኑሮአቸውን በምናኔ መድበው ቅዱሳት መጻሕፍት በማስተማር ደቀመዛሙርትን አፍርተው እምነትን በሥራ በመግለጻቸው በሞት ቢያልፉም ሥራቸው ሕያው ሆኖ በዚህ ክፍለ ዘመን ውጤቱን ለማየት በቅተናል።

ይሁን እንጂ ወጣቱ ትውልድ ስለ ሃይማኖትና ምግባር የሚያስተምረው በማጣቱ በየጊዜው እየኮበለለ ከከባድ የክህደትና የኑፋቄ አዘቅት ወድቆ ከእውነተኛው የተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር ተለይቶ ከጽድቅ ተርቦና ተጠምቶ እናየዋለን። ከፊሉ የማኒን ትምህርት ተከትለው «አልቦ እግዚአብሔር» ብለው ለዚች ዓለም ሠራዒ መጋቢ የላትም ውኆች በዘልማድ ይፈሳሉ፣ ነፋሳት በዘልማድ ይነፍሳሉ፣ ብርሃናት በዘልማድ ይመላለሳሉ፣ መዓልትና ሌሊት፣ በጋና ክረምት በዘልማድ ይፈራረቃሉ፣ ትንሣኤ ሙታን ነፍስ ጽድቅና ኩነኔ የለም ወዘተ ወደሚሉ ሲነጉዱ፣ ብዙ ሕዝብ ደግሞ የአርዮስን፣ የመቅዶንዮስን፣ የልዮንንና የመሳሰሉትን የመናፍቃን ትምህርት ሰምተው አምላክ ሥላሴ አይደለም አንድ አካል አንድ ገጽ ነው፣ ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ አይደለም አካል የሌለው ኃይል ነው ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል አይደለም፣ ድንግል ማርያም አታማልድም፣ የዘወትር ድንግል አይደለችም በሚለው የስህተት ትምህርት ተሰበው በልዩ ልዩ የመናፍቃን ድርጅቶች ገብተዋል። ሌሎች ደግሞ ለጨሌ፣ ለዛር አንጋሽ፣ ለቃልቻ እየሰገዱ ለአጋንንት እየገበሩ በዘልማድ ይመላለሳሉ። ይኽንና ይኽን የመሳሰለውን ስንመለከት ከእውነተኞች ክርስቲያኖች እጅግ ብዙ እንደሚጠበቅ ለመገንዘብ እንችላለን።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ነን ካልን እምነታችንን ለማጠናከር በስብከተ ወንጌል እየተሳተፍን ስለ ሃይማኖታችን ማወቅና መረዳት ያስፈልገናል። በስም ብቻ ሃይማኖት አለን እያልን ከተቀመጥን በተኩላ ከመነጠቅ አናመልጥም። የቤተክርስቲያን ህልውና እንዲጠበቅ በገንዘብ፣ በሐሳብና በጉልበት መሥዋዕት መሆን የምንችለው መጀመሪያ ስለ ሃይማኖታችን ስናውቅ ነው። አለበለዚያ በልማድ እኛ ክርስቲያን ነን ማለት ከንቱ ነው። ሬሳ ለመቅበር ዕድር፣ ገንዘብ ለማግኘት ዕቁብ፣ ለመረዳዳት የቤተዘመድን፣ የጓደኝነት የመረዳጃ ማኅበር እያቋቋምን ለሥጋችን ሌት ተቀን ስንሯሯጥ እንገኛለን፣ ድርጊቱ የሚያስተች አይደለም ነገር ግን ለነፍሳችን ደግሞ ልናስብ ይገባናል።

## ማስተካከያ

በ፲ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ዕትማችን በገጽ ፴፩ ላይ ኑ! የእግዚአብሔርን ቤት እንሥራ፤ በሚለው ርዕሳችን ሥር ባቀረብነው ጽሑፍ ለደሴ መርቆሬዎስ ቤተክርስቲያን ዕርዳታ ለመስጠት የምትሹ የባንክ ቁጥር 2871822 ተብሎ የተገለጸው በስህተት ስለሆነ ስለ ስህተቱ ይቅርታ እየጠየቅን ትክክለኛው የባንክ ሂሳብ ቁጥር 14321 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደሴ ቅርንጫፍ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

ሌሎቹን ማዳን የምንችለው እኛ ስለ ሃይማኖታችን በቂ እውቀት ሲኖረን ነውና በየአጥቢያ ቤተክርስቲያኑ ስብከተ ወንጌልን እየተካፈልን ለዘለዓለ ማዊት ቤታችን (ገነት) መንግሥተ ሰማያት፣ ለቤተክርስቲያን ህልውና፣ ጠቃሚ ለሆነው ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት እንደየስጦታችን እምነታችንን በሥራ ለመተርጐም ታጥቀን መነሣት ይኖርብናል።

ሐዋርያው ያዕቆብ እምነት ከሥራ ተለይቶ ጥቅም እንደማይሰጥ ገልጦ አስተምሮናልና ልብ ገዝተን ለእናታችን ቤተክርስቲያን የተግባር ተቆርቋሪዎች ለመሆን እንብቃ!!

"እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ መልካም ታደርጋለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጣል፣ አንተ ከንቱ ሰው እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" ያዕ ምዕ ፪ ቁ ፲፱፡፳፡፳፮ ስለዚህ በየጊዜው ስብከተ ወንጌልን እየተከታተልን ለስብከተ ወንጌል መጠናከር በልባዊ ጸሎትና በሌሎቹም መንፈሳዊ ትሩፋቶች ተጋድሎዋችንን መቀጠል ይጠበቅብናልና። እምነታችንን በሥራ ለመግለጽ ኃያል አምላክ የባሕርዩ ጌታ መድኅኒ ዓለም ክርስቶስ ይርዳን አሜን።



www.ethiopisnorthodox.org

# ዓምደ ሃይማኖት

## መንፈስ ቅዱስ ከማን ሠረጸ? ከአብ ብቻ ወይስ ከወልድም

በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት እንደ ሚታወቀው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብለን ከምንጠራቸው ከሦስቱ መለኮታዊ አካላት ሦስተኛው አካል መንፈስ ቅዱስ በተለይ ግብሩ ሠራጺ በመባል ይታወቃል። በባሕርዩም ሕያው ወማኅየዊ ነው። ይኸም ማለት ሕያውነት ያለው ሲኾን ይኸንኑ ሕያውነቱን በጸጋ ለፍጡራን ስለሚሰጥ ማኅየዊ ይባላል። አዳኝ ሕይወትን ሰጪ ማለት ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርጸት ማለትም መሥረጽ መውጣት መገኘት በጥልቀት ከማየታችን በፊት ሠራጺነት የሚለውን ቃል ፍችውን እንመልከት።

ሠራጺ፣ የሚለው ቃል ሠረጸ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው።
ሠረጸ– ወጣ፣ በቀለ፣ ተገኘ፣ ማለት ሲኾን ሠራጺ ሲል የሚሠርጽ፣ የሚወጣ፣ ወጪ ማለትን ያሳያል።

ለዚህም ትርጉም የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ምስክርነት ስለሚያስፈልግ የቅዱስ አትናቴዎስንና የቅዱስ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢን ቃል ዋቢ እናደርጋለን። ቅዱስ አትናቴዎስ "መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ወኢእሥራጺ" ብሏል። ቅዱስ ያዕቆብም "ከዊነ ሠራጺ ለመንፈስ ቅዱስ ባሕቲቱ" ይላል። የሁለቱም ትርጉም በአማርኛ "መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላል አሥራጺ አይባልም አይደለም። የሠራጺነት ከዊን ወይም ሠራጺ መኾን የብቻው የመንፈስ ቅዱስ ግብር ነው" ማለት ነው።

ሥርጸት /Procesoion/ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ግብር ስለኾነ በዚህ መለኮታዊ ግብር ማለትም በሠራጺነት አብና ወልድ አይሳተፉም። ይኸም ማለት ሁለቱ አካላት አብ ወልድ በሕልውና ከመንፈስ ቅዱስጋር የሚገናዘቡ በሕልውና አንድነት ያላቸው ሲኾኑ በአካላዊ ግብር ግን እንደ መንፈስ ቅዱስ አይሠርጹም ወይም ሠራጺነት የላቸውም። ምንጊዜም ለዘላለም ሥላሴ በአካላት ግብር ልዩነት ስላላቸው በአካላዊ ግብር ሦስት ይባላሉ። የአካል ግብር ተብለው የሚታወቁትም ውስጣዊ ግብሮች፣ መውለድ ማሥረጽ፣ መወለድና መሥረጽ ናቸው። በሌላ አነጋገር ወላዲነት አሥራጺነት፣ ተወላዲነት ሠራጺነት ተብለው የሚጠሩት ናቸው። ሥላሴ በእንደነዚህ ያሉት አካላዊ ግብሮች ልዩነት እንጂ አንድነት የላቸውም። የሥላሴ አንድነታቸውም በሕልውና ተገናዝበው በሚሠሩት አምላካዊ ግብር ተብለው በሚታወቁት የባሕርይ አንድነታቸው በመፍጠር በመግዛት፣ በማዳንና በመፍረድ፣ በመስጠትና በመንሳት ይኸን በመሳሰሉ ጠባይዓት ነው።

ስለዚህ ነው በተለየ ስሙ መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ ተፈናዊ /ተላኪ/ በተለየ ባሕርዩ ሕያው ማኅየዊ ሲሆን በተለየግብሩ ሠራጺ የሚባለው። በመለኮትና በሕልውና ወይም ሦስቱን አካላት አንድ አምላክ በሚያሰኝ የባሕርይ አንድነት ካልኾነ ሠራጺነት አብና ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አይሳተፉም። ወይም በሌላ አነጋገር አብ ወልድ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺነት የላቸውም አይሠርጹም ማለት ነው።

የሥላሴን የአካላት ግብር ሊቃውንት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ተርጉመዋል ጽፈዋል፣ መስክረዋል። ለምሳሌ ቅዱስ ቴዎዶስዮስ እንዲህ ሲል ይመሰክራል "አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ" ትርጉሙም "አብ ወላጅ ነው፣ ወልድ ተወላጅ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ የወጣ ነው" ማለት ነው።

ሱንትዮስ የተባለው ሊቅም "ነአምን በአብ በሥርዓተ አብና ወለ ወልድኒ በሥርዓተ ወልድና ወለመንፈስ ቅዱስኒ በሥርዓተ ሥርጽና" ብሏል ይኸም ሲተረጎም "አብን በአባትነት ሥርዓት አባት ነው ብለን እናምናለን። ወልድንም በልጅነት ሥርዓት ልጅ ነው ብለን እናምናለን። መንፈስ ቅዱስንም በመሥረጽ/በመገኘት፣ በመውጣት/ ሥርዓት ሠራጺ ነው ብለን እናምናለን" ማለት ነው።

የአብ ግብሩ መውለድ ማሥረጽ ነው። ወልድን ይወልዳል መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻል ስለዚህም አብ በአካላዊ ግብሩ ወላዲ አሥራጺ ይባላል። የወልድ ግብሩ መወለድ ነው ከአብ ይወለዳል ስለዚህም ተወላዲ ይባላል። የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረጽ ነው ከአብ ይሠርጻል። ስለዚህም ሠራጺ ይባላል።

አብ እንደ ወልድ ተወላዲ እንደመንፈስ ቅዱስ ሠራጺ አይባልም ለዘላለሙ ወላዲ አሥራጺ ይባላል እንጂ። ወልድም እንደ አብ ወላዲ አሥራጺ እንደመንፈስ ቅዱስም ሠራጺ አይባልም ለዘላለሙ ተወላዲ ይባላል እንጂ። መንፈስ ቅዱስም እንደአብ ወላዲ አሥራጺ እንደወልድም ተወላዲ አይባልም ለዘላለሙ ሠራጺ ይባላል እንጅ። እንዲህ ስለተባለ ግን በዚህ ዓለም ሥርዓት በሕገ ተፈጥሮ ወላጅ ከተወላጅ እንደሚቀድም እንደሚበልጥ ወይም የተገኘ (የወጣ) ከአስገኚው ወደኋላ እንደሚል እንደሚያንስ የሥላሴ ግብር በዚህ ዓይነት አይመስልም አይተ



www.ethiopisnorthodox.org

ረጎምም በሥላሴ ዘንድ መቅደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ የለምና ስለኾነም አባቶቻችን ሊቃውንት እንዳስተማሩን እናምናለን እንታመናለን።

"እሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና እሐቲ ክዋኒሆሙ ለሥላሴ ለሥላሴ አልቦሙ ሰዓት ከመቅጽበተ ዓይን" /ኤራቅሊስ/ "ኢሀሎ አብ ዘመነ ዘእንበለ ወልድ ወኢሃሎ ወልድ ዘመነ ዘእንበለ መንፈስ ቅዱስ ኢእሐተ ሰዓተ ወኢቅጽበተ "ዓይን /ሠለስቱ ምእት/ ትርጉማቸው እነሆ የሥላሴ" ቅድምናቸው አንዲትናት በቅድምና ትክክል አንድ ናቸው። የሥላሴ ከዊናቸው። /በሦስትነት የመገኘታቸው/ አንዲት ናት ለሥላሴ አንድ ሰዓት እንኳን የዓይን ጥቅሻ ያህል መቀዳደም የለባቸውም። አባት ያለ ልጅ ብቻውን የኖረበት ዘመን ወልድም ያለ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰዓት እንኳ የዓይን ጥቅሻ ያሕል ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም።"

እግዚአብሔር አብ ለዘላለም በወላዲነት በእሥራጺነት ግብሩ አለ ይኖራል። እግዚአብሔር ወልድም ለዘላለሙ በሠራጺነት ግብሩ አለ ይኖራል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ለዘላለም በተወላዲነት

ግብሩ አለ ይኖራል። የአካላት ግብር ለዘላለሙ ጥንትና ፍጻሜ ሳይኖረው ከተመትሮ ከተፈልጦ፣ ከተድኅሮ፣ የተለየ ኾኖ ያለ ማቋረጥ ሲፈጸም የሚኖር እንጂ በሕገ ተፈጥሮ በሰው አኗኗር በስነ ፍጥረት ጠባይ እንደሚታወቀው አይደለም። በፍጥረት ሕግ በሰብአዊ ጠባይ አባትነትና ልጅነት ማስገኘትና መገኘት ተለዋዋጭና መቀዳደም መከታተል ያለበት ሲሆን መለየትና መቋረጥን የሚያስከትል ነው። በሥላሴ ዘንድ ግን ያለው የአካላት ግብር እንደዚህ አይደለም በስነፍጥረት አይመሰልም ተመሳሳይ ተወዳዳሪ አይገኝለትም። ለምሳሌ በሰው ዘንድ ያለውን የተፈጥሮ ጠባይ ብንወስድ ልጅ የነበረው በወለደ ጊዜ አባት ይባላል። ልጅ ሳለ አባት አይባልም ልጅ የነበረው ከወለደ በኋላ ግን ወላጅ ይባላል። ለወለዱት ልጅ ለወለደው ወይም ለወላጆቸው ግን አባት ሲባል ይኖራል። በወለጆቹ ሰውነት ሳለ ግን በዘር በሩካቤ ከመፀነሱ ከመወለዱ በፊት የልጅነትም ሆነ የአባትነት ስያሜ አልነበረውም ገና አልተፈጠረም አልተወለደም ልጅም አባትም ሊባል አይቻልም። ከተወለደ በኋላ ግን ማለት ከአባት አብራክ ከእናት ማኅፀን ከተገኘ በኋላ ግን የልጅነትን ስያሜ ይወርሳል ከላይ እንደተባለው ወላጅ ሲሆንም በአባትነት ግብር ይታወቃል። በዚህም ስያሜ ወላጅ አባት ተብሎ ይጠራል። ከአባት አብራክ ከእናት ማኅፀን የተገኘ ልጅ ከወላጆቹ በዘመን ያንሳል ወደ ኋላ ይላል ወላጆቹ በተገኙ ጊዜ የተገኘ አይደለም ኑሮ ኑሮ በልደት የታወቀ ከወላጆቹ በኋላ ጊዜ የተገኘ ነው እንጂ። ስለዚህ የግድ ተፈልጦ ተመትሮ፣ ተከፍሎና ተድኅሮ ይከተተለዋል። ተከፍሎ ማለት ሰውነቱ ከእናትና ከአባቱ ተከፍሎ የተገኘ ስለሆነ ሁል ጊዜ በአባቱ አብራክ በእናቱ ደም ማኅፀን መኖር አይቻለውም። ተድኅሮ ማለት ከወላጆቹ በኋላ የተገኘ ስለኾነ በዘመን ከወላጆቹ ወደ ኋላ እንጂ ተስተካክሉ አይገኝም

ተፈልጦ ማለት በባሕርይም በአካልም ከወላጆቹ ይለያል እንደቀድሞው ከተወለደ በኋላ በእነርሱ ውስጥ መኖር አይቻለውም ተመትሮ ማለትም ራሱን ችሎ ይኖራል እንጂ በልጅነት ጠባይ ከወላጆቹ ጋር ያለው አኗኗር በባሕርይ ተዘምዶ ያለው አንድነት በፈቃድም ሆነ በስሜት በአካልም በባሕርይ ግንኙነቱ ይቋረጣል። በተለይም ልጅ የነበረው ሁል ጊዜ ልጅ ተብሎ አይኖርም አባት ወደ መባል ይለወጣል ይሸጋገራል። ይኸ ጠባይ በሥላሴ ዘንድ የለም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የአካላት ግብራቸው ስማቸው ሳይለወጥ አብም ወላዲ አሥራጺ እንደተባለ ይኖራል ወልድም ተወላዲ መንፈስ ቅዱስም ሠራጺ እንደተባሉ ይኖራሉ። ስለዚህም ሲያስረዳ ቅዱስ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት እንዲህ ብሏል። "አብሰ ኢተወልደ አላ ውእቱ ወላዲ ወልድ እምቅድመ ኵሉ ዓለም" አብስ አልተወለደም ከዓለም ፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ ወልድን የወለደው ነው እንጂ /አትና– ክፍል ፩/

የሥላሴን የአካላት ግብር አለመለዋወጥ፣ መከፈል፣ ወደ ኋላ ማለት፣ መለየትና መቋረጥ እንደሌለበት በፀሐይ ምሳሌነት ለማየት እንሞክር፣ ሥላሴ በፀሐይ ይመሰላሉ፣ ለፀሐይ ሦስት ነገር አላት ክበብ /አካል/ ጸዳል/ ብርሃን/፣ ዋዕይ/ሙቀት/ አላት። በክበቧ አብ በብርሃኗ ወልድ በሙቀቷ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ከፀሐይ ክበብ ወይም አካለ ብርሃንና ሙቀት ይወጣሉ ይገኛሉ። ለብርሃንና ለሙቀት አስገኝ አካል ፀሐይ ነው ማለት ክበቧ አካሏ ነው። እግዚአብሔር አብ በአካሏ ተመስሏል በብርሃን የተመሰለ ወልድን ይወልዳል በሙቀት የተመሰለ መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻል /ያስገኛል/ ብርሃንና ሙቀት ከፀሐይ ክበብ ይገኛሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ይወጣሉ /ይገኛሉ/ የወልድ ከአብ መገኘት መወለድ ሲባል የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት /መገኘት/ መሥረጽ ይባላል።

ፀሐይ በክበብነቷ ፣ በብርሃንነቷና በሙቀቷ ሳትለዋወጥ መለያየት ሳይገጥማት ከተፈጠረች ጊዜ አንሥቶ አለች። እስከታልፍ በዚሁ ዓይነት ትኖራለች። አብ በወላዲነቱ በአሥራጺነቱ ፤ ወልድም በተወላዲነቱ ፤ መንፈስ ቅዱስም በሠራጺነቱ ሳይለዋወጡ ይኖራሉ።

ከዚህ በላይ እንዳየነው አብ ወልድን ይወልዳል ፤ መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻል። ወልድም ከአብ ብቻ ይወለዳል። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ ይሠርጻል። የፀሐይ ክበብ ብርሃንን እንደሚወልድ ሙቀትን እንደሚያወርድ /እንደሚያስገኝ/ ብርሃንም ከፀሐይ ክበብ ብቻ እንደሚወለድ /እንደሚወጣ/ ሙቀትም ከፀሐይ ክበብ ብቻ እንደሚሠርጽ /እንደሚገኝ/ ማለት ነው። እስከዚህ ድረስ አብ ለወልድ መወለድ ፣ ለመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ምክንያት መሠረት መገኛ እንደኾነና ለእርሱ ግን ምክንያት እንደሌለው አይተናል። የአብን መሠረትነት ሲያስረዳ ዲዮናስዮስ ዘአርዮስፋጎስ "ልደተ ወልድ ወጻዓተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ኢይትነገር አላ



www.ethiopisnorthodox.org

ረኀምም በሥላሴ ዘንድ መቅደም መቀዳደም መብለጥ መበላለጥ የለምና ስለኾነም አባቶቻችን ሊቃውንት እንዳ ስተማሩን እናምናለን እንታመናለን።

"እሐቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ወዕሩያን እሙንቱ በቅድምና አሐቲ ክዋኒሆሙ ለሥላሴ ለሥላሴ አልቦሙ ሰዓት ከመቅጽበተ ዓይን" /ኤራቅሊስ/ "ኢሀሎ አብ ዘመነ ዘእንበለ ወልድ ወኢሃሎ ወልድ ዘመነ ዘእንበለ መንፈስ ቅዱስ ኢአሐተ ሰዓተ ወኢቅጽበተ "ዓይን /ሠለስቱ ምእት/ ትርጉማቸው እነሆ የሥላሴ" ቅድምናቸው አንዲ ትናት በቅድምና ትክክል አንድ ናቸው። የሥላሴ ከዊናቸው። /በሦስትነት የመገ ኘታቸው/ አንዲት ናት ለሥላሴ አንድ ሰዓት እንኳን የዓይን ጥቅሻ ያህል መቀዳደም የለባቸውም። አባት ያለ ልጅ ብቻውን የኖረበት ዘመን ወልድም ያለ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰዓት እንኳ የዓይን ጥቅሻ ያሕል ተለይቶ የኖረበት ዘመን የለም።"

እግዚአብሔር አብ ለዘላለም በወላ ዲነት በእሥራጺነት ግብሩ አለ ይኖራል። እግዚአብሔር ወልድም ለዘላለሙ በሠራጺነት ግብሩ አለ ይኖራል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ለዘላለም በተወላዲነት ግብሩ አለ ይኖራል። የአካላት ግብር ለዘላለሙ ጥንትና ፍጻሜ ሳይኖረው ከተመትሮ ከተፈልጦ፣ ከተድኅሮ፣ የተለየ ኾኖ ያለ ማቋረጥ ሲፈጸም የሚኖር እንጂ በሕገ ተፈጥሮ በሰው አኗኗር በስነ ፍጥረት ጠባይ እንደ ሚታወቀው አይደለም። በፍጥረት ሕግ በሰብአዊ ጠባይ አባትነትና ልጅነት ማስገኘትና መገኘት ተለዋዋጭና መቀዳደም መከታተል ያለበት ሲሆን መለየትና መቋረጥን የሚያስከትል ነው። በሥላሴ ዘንድ ግን ያለው የአካላት ግብር እንደዚህ አይደለም በስነፍጥረት አይመሰልም ተመሳሳይ ተወዳዳሪ አይገ ኝለትም። ለምሳሌ በሰው ዘንድ ያለውን የተፈጥሮ ጠባይ ብንወስድ ልጅ የነበረው በወለደ ጊዜ አባት ይባላል። ልጅ ሳለ አባት አይባልም ልጅ የነበረው ከወለደ በኋላ ግን ወላጅ ይባላል። ለወለዱት ልጅ ለወለደው ወይም ለወለ ዳቸው ግን አባት ሲባል ይኖራል። በወለጆቹ ሰውነት ሳለ ግን በዘር በሩካቤ ከመፀነሱ ከመወለዱ በፊት የልጅነትም ሆነ የአባትነት ስያሜ አልነበረውም ገና አልተፈጠረም አልተወለደም ልጅም አባትም ሊባል አይቻልም። ከተወለደ በኋላ ግን ማለት ከአባት አብራክ ከእናት ማኅፀን ከተገኘ በኋላ ግን የልጅነትን ስያሜ ይወርሳል ከላይ እንደተባለው ወላጅ ሲሆንም በአባትነት ግብር ይታወቃል። በዚህም ስያሜ ወላጅ አባት ተብሎ ይጠራል። ከአባት አብራክ ከእናት ማኅፀን የተገኘ ልጅ ከወላጆቹ በዘመን ያንሳል ወደ ኋላ ይላል ወላጆቹ በተገኙ ጊዜ የተገኘ አይደለም ኑሮ ኑሮ በልደት የታወቀ ከወላጆቹ በኋላ ጊዜ የተገኘ ነው እንጂ። ስለዚህ የግድ ተፈልጦ ተመትሮ፣ ተከፍሎና ተድኅሮ ይከተተለዋል። ተከፍሎ ማለት ሰውነቱ ከእናትና ከአባቱ ተከፍሎ የተገኘ ስለሆነ ሁል ጊዜ በአባቱ አብራክ በእናቱ ደም ማኅፀን መኖር አይቻ ለውም። ተድኅሮ ማለት ከወላጆቹ በኋላ የተገኘ ስለኾነ በዘመን ከወላጆቹ ወደ ኋላ እንጂ ተስተካክሉ አይገኝም

ተፈልጦ ማለት በባሕርይም በአካልም ከወላጆቹ ይለያል እንደቀድሞው ከተወለደ በኋላ በእነርሱ ውስጥ መኖር አይቻለውም ተመትሮ ማለትም ራሱን ችሎ ይኖራል እንጂ በልጅነት ጠባይ ከወላጆቹ ጋር ያለው አኗኗር በባሕርይ ተዘምዶ ያለው አንድነት በፈቃድም ሆነ በስሜት በአካልም በባሕርይ ግንኙነቱ ይቋረጣል። በተለይም ልጅ የነበረው ሁል ጊዜ ልጅ ተብሎ አይኖርም አባት ወደ መባል ይለወጣል ይሸጋገራል። ይኽ ጠባይ በሥላሴ ዘንድ የለም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የአካላት ግብራቸው ስማቸው ሳይለወጥ አብም ወላዲ አሥራጺ እንደተባለ ይኖራል ወልድም ተወላዲ መንፈስ ቅዱስም ሠራጺ እንደተባሉ ይኖራሉ። ስለዚህም ሲያስረዳ ቅዱስ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት እንዲህ ብሏል። "አብሰ ኢተወልደ አላ ውእቱ ወላዲ ወልድ እምቅድመ ኵሉ ዓለም" አብስ አልተወለደም ከዓለም ፍጥረት ሁሉ አስቀድሞ ወልድን የወለደው ነው እንጂ /አትና– ክፍል ፬/

የሥላሴን የአካላት ግብር አለመለ ዋወጥ፣ መከፈል፣ ወደ ኋላ ማለት፣ መለየትና መቋረጥ እንደሌለበት በፀሐይ ምሳሌነት ለማየት እንሞክር፣ ሥላሴ በፀሐይ ይመሰላሉ፣ ለፀሐይ ሦስት ነገር አላት ክበብ /አካል/ ጸዳል/ ብርሃን/፣ ዋዕይ/ሙቀት/ አላት። በክበቧ አብ በብርሃኗ ወልድ በሙቀቷ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል። ከፀሐይ ክበብ ወይም አካለ ብርሃንና ሙቀት ይወጣሉ ይገኛሉ። ለብርሃንና ለሙቀት አስገኝ አካል ፀሐይ ነው ማለት ክበቧ አካሏ ነው። እግዚአብሔር አብ በአካሏ ተመስሏል በብርሃን የተመሰለ ወልድን ይወልዳል በሙቀት የተመሰለ መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻል /ያስገኛል/ ብርሃንና ሙቀት ከፀሐይ ክበብ ይገኛሉ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ይወጣሉ / ይገኛሉ/ የወልድ ከአብ መገኘት መወለድ ሲባል የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት /መገኘት/ መሥረጽ ይባላል።

ፀሐይ በክበብነቷ ፣ በብርሃንነቷና በሙቀቷ ሳትለዋወጥ መለያየት ሳይገ ጣማት ከተፈጠረች ጊዜ እንሥቶ አለች። እስከታልፍ በዚሁ ዓይነት ትኖራለች። አብ በወላዲነቱ በአሥራ ጺነቱ ፣ ወልድም በተወላዲነቱ ፣ መንፈስ ቅዱስም በሠራጺነቱ ሳይለ ዋወጡ ይኖራሉ።

ከዚህ በላይ እንዳየነው አብ ወልድን ይወልዳል ፣ መንፈስ ቅዱስን ያሠርጻል። ወልድም ከአብ ብቻ ይወለዳል። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ ይሠርጻል። የፀሐይ ክበብ ብርሃንን እንደሚወልድ ሙቀትን እንደሚያወርድ /እንደሚያ ስገኝ/ ብርሃንም ከፀሐይ ክበብ ብቻ እንደሚወለድ /እንደሚወጣ/ ሙቀትም ከፀሐይ ክበብ ብቻ እንደሚሠርጽ /እንደሚገኝ/ ማለት ነው። እስከዚህ ድረስ አብ ለወልድ መወለድ ፣ ለመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ምክንያት መሠረት መገኛ እንደኾነና ለእርሱ ግን ምክንያት እንደሌለው አይተናል። የአብን መሠረ ትነት ሲያስረዳ ዲዮናስዮስ ዘአርዮስ ፋጎስ "ልደተ ወልድ ወጸዓተ መንፈስ ቅዱስ እምአብ ኢይትነገር አላ



www.ethiopisnorthodox.org

ይትነከር" ብሏል። ይኸም ማለት ከአብ የወልድ መወለድ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ይደነቃል ዕፁብ ዕፁብ ይባላል እንጂ አይነገርም አይመረ መርም ማለት ነው።

ለወልድ መወለድ ለመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ መሠረቱ ምክንያቱ መገኛው አብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም የአብን መሠረትነት ይገልጻል። ወልድ ከአብ መወለዱን /መውጣቱን/ መንፈስ ቅዱስም ከአብ መሥረጹን /መገኘቱን/ ያስረዳል። "ወለድኩከ እመከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ" /መዝ ፩፻፱ ቁጥር ፫/ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ባሕርይ ዘእምባሕርይ አካል ዘእም አካል ወለድኩህ ይላል። አብ ወልድን የወለደ ወልድም ከአብ የተወለደ መኾኑን ያስረዳል። "ወሶበ መጽአ ጰራቅሊጦስ ዘአነ እፌኑ ለክሙ ዘይወጽእ እምአብ ውእቱ ሰማዕትየ" "ከአብ የሚወጣ እኔ የምልክላችሁ ጰራቅሊጦስ በመጣ ጊዜ ምስክሬ ነው" /ዮሐ ፲፭ ቁጥር ፳፮/

መንፈስ ቅዱስ ከአብ እንደሠረጸ /እንደወጣ/ አብ መንፈስ ቅዱስን እንዳ ሠረጸ /እንዳስገኘ/ የሚያስረዳ ነው። "እምኀበ እግዚአብሔር ወጻእኩ ወመጻእኩ ውስተ ዓለም" /ዮሐ ፲፮ ቁ. ፳፰/ ትርጉም "ከአብ ወጣሁ ወደ ዓለም መጣሁ" ማለት ነው። ይኸውም ወልድ ከአብ የወጣ /የተወለደ/ ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ ወደ ዓለም የመጣ የተገለጸ መኾኑን ይመሰክራል። የአብን ወላዲነት የወልድን ተወላዲነት ከማረጋ ገጡም በላይ አብ ወልድን በመውለዱ ለውልድ መገኘት መሠረቱ እሱ መሆኑን ያስገነዝባል።

ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና በቅዱሳን ሊቃውንት ምስክርነት የሥላሴ መሠረት አብ መኾኑንና ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ መገኘታ ቸውን በመረጃዎቹ ተገንዝበናል።

በቤተክርስቲያን ታሪክም በተደ ረገው ዓለም አቀፋዊ የሲኖዶስ ውሳኔ የተረጋገጠው ይኸው እውነት ነበር። መቅዶንዮስ የተባለው ፀረ መንፈስ ቅዱስ ቁጥሩ ከመንፈቀ አርዮሳውያን የነበረው የቁስጥንጥንያ ሊቀጳጳስ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነትና ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን የክብር የጌትነት አንድነት ክዶ በተነሣ ጊዜ እርሱን ለማውገዝ ቤተክርስቲያን በቁስጥን ጥንያ ጉባኤ አድርጋ ነበር። የተሰበሰ ቡትም ሊቃውንት /ሊቃነ ጳጳሳት/ ቁጥራቸው ፩፻፶ ይሆናል። ከመጻሕፍት ጠቅሰው ምላሽ ካሳጡት በኋላ አልመ ለስም ብሎ እንደ አርዮስ በክህደቱ ፀንቶ በመገኘቱ እርሱንም ትምህርቱንም ከአወገዙ በኋላ ከሠለስቱ ምዕት የሃይ ማኖት ቀኖና ጋር አንድ አድርገው ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚከተለውን የሃይ ማኖት አንቀጽ አስተላለፉ። ጉባኤውም የተደረገበት ዘመን በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ፫፻፸፫ ዓ.ም. ሲሆን በአውሮ ፓውያን በ፫፻፹፩ ዓ.ም. ነው።

## የቁስጥንጥንያ የሃይማኖት ውሳኔ ስለ መንፈስ ቅዱስ

"ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት" ትርጉሙም እነሆ "በጌታ በአዳኝ ከአብ በሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እንሰግድለት እናመስ ግነው።" ወይም "በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረጸ ፤ ከአብና ከወልድ ጋር ባንድነት እንሰግድለታለን ፤ እናመ ሰግነዋለንም። ርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው። /ጸሎተ ሃይማኖት/ ማለት ነው። የሁለቱም አተረጓጐም ምሥጢር አያዛባም የአማርኛ ስልት ልዩነት ብቻ ይኖረዋል። የግዕዙ ንባብ ግን ያው ነው ልዩነት የለውም። በመግ ቢያው ርእስ ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ከማን እንደኾነ ምላሽ እንዲሰጥ በጥያቄ መልክ ቀርቧል። ጥያቄው መንፈስ ቅዱስ ከማን ሠረጸ? ከአብ ብቻ ወይስ ከወልድም? የሚል ነው። ከሊቃውንት ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሁለተኛው የዓለም አቀፍ የቤ ተክርስቲያን ጉባኤ የሲኖዶስ ውሳኔ እንደተመለከትነው ከኾነ ምላሹ ተሰጥቷል። ሌላ የሚያነጋግር ፤ የሚያጠ ያይቅ ጉዳይ አይኖርም። መንፈስ ቅዱስ የሠረጸው ከአብ ብቻ ነው እንጂ ከወልድም ሠረጸ ማለት አይቻልም። ከመጽሐፍ ቅዱስና ከጥንታዊት ቤተክር ስቲያን ዓለም አቀፋዊ የሃይማኖት ቀኖና ውጭ መንፈስ ቅዱስ ከውልድም ሠረጸ ማለት ድፍረትም ክህደትም ነው። ይሁን እንጂ ደፋሮች ስለማይጠፉ በልብ ወለድ ፈጠራ የቤተክርስቲያንን አንድነት የሚከፋፍሉ አሉ። ቤተክርስ ቲያን ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና በቅዱሳን አበው ሊቃውንት ጉባኤ የተ ወሰነውን ዘሠረጸ እምአብ /ከአብ የሠረጸ/ የሚለውን ቀኖና የሃይማኖት ዶግማ ተቀብላ አምናና አሳምና ትኖራለች።

ተከታዩን ክፍል ይዘን እስክንቀርብ ላችሁ ድረስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርጸት የተሰጠውን ትምህርት እያጣጣማችሁ ቆዩልን። እግዚአብሔር ከአበው ሃይማኖት ፤ ከቤተክርስቲያን ኦርቶዶ ክሳዊ ትምህርት እያናውጸን አሜን።

አባ ጳኩሚስ በአንዲት ቤት ለአጋንንት ወፍረው ባት አየ። ጥንቱን ሰው ደካማ ነው ፤ በዚያውም ላይ በቤቱ በሕርይ ይህ ተጨምሮ እንደምን ይቻላል ፤ ወደ፤ መለሰው ብሎ ጸለየ። የንድ ቀሮንብ ወዳንዱ ቀሮ፤ የንድ ማድጋ ወሀ ወዳንዱ ማድጋ እንዲገለበጥ ፤ በሏ ከፍረው የነበሩ አጋንንት ወደሱ መጡ። ሜቅ ምንጣፍ ለብሰ፤ ከመድ ላይ ተኝቶ የማስናቸው ጀመረ። ከዚህ በኋላ "እንሒድ እንጂ እንሒድ እንጂ" ሲሉ ሰማቸው። "ሰው ከወዳጁ ቤት ውሎ አይደር አይሔደምን፤ እናንተስ አትቆዩምን?" አላቸው። "ከነኑ ከስወጣነው ከአዳም ልጆች እንዲህ ያለ አርበኛ አይተን አናውቅም" ብለው አጋንንቱ የአባ ጳኩሚስን ቅድስና መስክረዋል።

እናስ ለወንድሞቻችንና እህቶቻችን እስከምን ድረስ እንራራለን?

መጽሐፍተ መነኮሳት

አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን ፲፭ ተመልከት



www.ethiopisnorthodox.org

www.ethiopisnorthodox.org